በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ልማት ቢሮ

በመጠጥ ውሃ ተቋማት አስተዳደር ፣ ጥገና እና የመለዋወጫ አቅርቦት ወጣቶች የስራ እድል ተጠቃሚ ለማድረግ የወጣ አሰራር

1.መግቢያ

- በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የወጣው የውሃ ሀብት አስተዳደር ፖሊሲ የገጠር መጠጥ ውሃ ተቋማት አያያዝ፣አጠቃቀምና ማስተዳደርን በተመለከተ በግልፅ አስቀምጧል፡፡ በፖሊሲ ውስጥ ለገጠር መጠጥ ውሃ ኦፕሬሽንና ጥገና በተመለከተ ከተቀመጡት መርሆዎች ዋና ዋናዎቹ፡-
- ነባር የውሃ ተቋማትን መንከባከብና ውሃውን በቁጠባ መጠቀም አዲስ የውሃ ተቋማትን ከማልማት ያልተናነሰ ጥቅም ሰጪ መሆኑን ማራመድና ማበረታታት፤
- የውሃ ተቋማት አስተማማኝና ዘለቄታዊ አገልግሎት እንዲሰጡ የተቀናጀ የኦፕሬሽንና ጥገና ማዕቀፍ እንዲኖር ማበረታታት፤
- በውጪ ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች በብድርና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በመንግስትም የሚካሄዱ ፕሮጀክቶችና የልማት ተግባራት ሁሉ ለአስተማማኝ ኦፕሬሽንና ጥገና ራስ አገዝ ከራስ ገቢ የሚሸፈን የልማት በጀት እቅድ እንዲኖራቸው ማረጋገጥ፤

- ሕብረተሰቡ በተለይም ሴቶች በውሃ ተቋማት በኦፕሬሽንና ጥገና ተግባራት ላይ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማበረታታት።

- የውሃ ተቋማት በኦፕሬሽንና ጥገና ዘለቄታዊነትን በሚያጎለብት መልኩ ባልተማከለ አሰራር ላይ የተመረኮዘ እንዲሆን ማበረታታት።

- ለገጠር የህብረተሰብ ክፍሎች ለውሃ ተቋም ግንባታ ወጪ የሕብረተሰቡ አቅም እስካልቻለ ድረስ መሠረታዊ የውሃ ፍላጎታቸውን ለማርካት የኦፕሬሽንና ጥገና ወጪውን እንዲሸፍኑ ሆኖ የአገሪቱ ኢኮኖሚ አቅም በሚፈቅደው መጠን የግንባታው ወጪ መንግሥት እንዲሸፍን ማድረግ።

- ከላይ በፖሊሲው የተቀመጡትን መርሆዎች መሠረት በማድረግ ተግባራትን እያከናወነ ያለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የውሃ መስኖና ኢነርጂ ልማት ቢሮ በአዋጅ ቁጥር 188/2003 ዓ.ም በአንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 12 ከተሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶች እና የገጠር የንጹህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበር አደረጃጀትና አሰራር መመሪያ ቁጥር 03/2007 መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

- በክልላችን በገጠርም ሆነ በከተሞች ያሉት የውሃ ተቋማትን የብልሽት ምጣኔን በከፍተኛ ደረጃ በመቀነስ እና ሲበላሹም በጥራትና በሚፈለገው የመለዋወጫና የመገጣጠሚያ እቃዎች በአፋጣኝ በመጠገን ለህብረተሰቡ ተጠቃሚ ለማድረግ በወረዳ ደረጃ ራሱን የቻለ አቅራቢ ደረጅት ባለመኖሩ መሰረታዊ መፍትሄ የሚፈልግ ጉዳይ ሆኗል፡፡

- በዚህ መሰረት የገጠር መጠጥ ውሃ የስፔር ፓርት አቅርቦት በዋናነት በወረዳ ደረጃ መኖር እንዳለበትና ተጠቃሚዎችም ሆኑ ሌሎች አካላት ለመጠጥ ውሃ ጥገና ስራ ከነዚሁ አቅራቢዎች መግዛት ይኖርባቸዋል፡፡ ስለሆነም የመለዋወጫና የመገጣጠሚያ ዕቃዎችን ለህብረተሰቡ በማቅረብ ተጠቃሚዎችን በማርካት ወጣቶችን ተጠቃሚ ማድረግ ነው፡፡

2. የመጠጥ ዉሀ ተቋማት ግንባታ በተመለከተ

- በክልላችን አንስተኛ የመጠጥ ዉሀ ተቋማት እስከ 2007 ዓ.ም 66,102 ተገንብተዋል ፡፡
- በገጠር አነስተኛ የውሃ ተቋማት ለመገንባት በስራው ላይ የተሰማሩት ስራ የሌላቸዉ ወጣቶች ናቸው፡፡

- በተለይም ስራ የሌላቸው ወጣቶችን በማህበር በማደራጀት በፍላጎት በራሳቸዉ ወጭ ለ45 ቀን በማሰልጠን የአርቴዠያ ፍቃድ በመስጠት ወደ ስራ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡

- በክልላችን እስከ 2008 ዓ.ም 4809   ስራ የሌላቸዉ ወጣቶች አርቴዥያን እንዲሰለጥኑ ተደርጓል፡፡ እነዘህን በአርቴዥያን የሰለጠኑ ወጣቶች በአንስተኛ የውሃ ተቋማት ግንባታበእጅ ዋጋ ብቻ እነዲሳተፉ ተደርጓል፤፤

3. ነባር የመጠጥ ውሃ ተቋማት አስተዳደር፣ጥገና እና በመለዋወጫ አቅርቦት በተመለከተ

- በገጠር 66,102 አነስተኛ የውሃ ተቋማት እስከ 2007ዓ.ም ተገንብተዋል፡፡
- ከተገነቡት የዉሃ ተቋማት ውስጥ 4777 አገልግሎት አይሰጡም፡፡

የዉሃ ተቋማት አገልግሎት ያቋረጡበት ምክንያቶች

- የውሃ ተቋማት ሲበላሹ በአካባቢው ስፔር ፓርት አቅርቦት አለመኖር
- በተጠቃሚው ስፔር ፓርት ገዝቶ ለመጠገን ፍላጎት አለመኖር፣ በመንግስት ይጠገ ናል የሚል አመለካከት መኖር
- የውሃ ተቋማት ሲበላሹ የሚጠግን በቀበሌ /በዉሃ ተቋም /ባለሙያ አለመኖር እንዲሁም ለኮሚቴ በጥገና ላይ ስልጠና አለመስጠት

- የዉሀ ተቋማቱን የሚያስተዳድር ባለቤት የሌለው መሆኑ የውሃ ኮሚቴዎች ከተጠቃሚዎች የተመረጡ በየግል ሥራቸው በመሄድ ትኩረት አለመስጠት
- የውሃ ኮሚቴው ወቅታዊ የሆነ ስልጠና ያለማግኘት

- የውሃ ኮሚቴውን ከተጠቃሚው የሚሰበሰበውን ገንዘብ በደረሰኝ አለመቀበል ፤ በአግባቡ አለመያዝ ፤ማጥፋት፤ተጠያቂ የሚሆኑበት ሰርዓት አለመኖር

- የውሃ ተቋማትን እንዲታጠሩ እና ዘበኛ እንዲኖራቸው በማድረግ በኩል ተጠቃሚዉ ባለቤት አለመሆን

- የውሃ ተቋማት በሚገነቡበት ጊዜ ተጠቃሚው በግንባታ ባለማሳተፍ ባለቤት ያለማድረግ ችግር

4. በመጠጥ ዉሃ ተቋማት አስተዳደር ዙሪያ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት የተወሰደ መፍትሄ

- በቢሮ በኩል ቀድሚያ ተግባር ደህንን ችግር የሚፈታ የአሰራር መመሪያ ማውጣት ነው፡፡
- በገጠር የአነስተኛ የውሃ ተቋማት ለሚያስተዳድርና ተቋማትን በዘላቂነት እንዲያገለግሉ ለማድረግ በቢሮ በኩል የገጠር መጠጥ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት አደረጃጀት እና አሰርር መመሪያ በ2007 ዓ.ም ወጥቶ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡
- የገጠር መጠጥ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት መመሪያ ማውጣት ያስፈለጋል ምክንያት

- ማህበራቱ የቆጥር ሰራተኞች በመቆጠር ተቋማት ዘለቄታዊነት አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ እና በዉሃ ዘርፍ ለተመረቁ ወጣቶች የስራ እድል ለመፍጠር

- የውሃ ኮሚቴን ህጋዊ ሰውነት መስጠት ተቋማት በባለቤትነት እንዲይዛቸዉ ማድረግ

- የውሃ ተጠቃሚዎች የኦፕሬሽንና ጥገና ገንዘብ እንዲያወጡ በማድረግ ተቋማት ሲበላሹ ጥገና እንዲደረግላቸው በማድረግ ዘለቄታዊ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ

5. የገጠር መጠጥውሃ ተጠቃሚዎችን ማህበራት አደረጃጀት በተመለከተ 8 ደረጃዎች አሉት

- ደረጃ “ሀ”፤ የዉሃ ተቋሙ ቀበሌ አገናኝ ሆኖ ስድስት እና ከዚያ በላይ ቀበሌዎችን የሚያገናኝ ከሆነ
- ደረጃ “ለ”፤ የዉሃ ተቋሙ ቀበሌ አገናኝ ሆኖ አምስት ቀበሌዎችን የሚያገናኝ ከሆነ
- ደረጃ “ሐ”፤ የዉሃ ተቋሙ ቀበሌ አገናኝ ሆኖ አራት ቀበሌዎችን የሚያገናኝ ከሆነ
- ደረጃ “መ”፤የዉሃ ተቋሙ ቀበሌ አገናኝ ሆኖ ሶስት ቀበሌዎችን የሚያገናኝ ከሆነ
- ደረጃ “ሠ”፤የዉሃ ተቋሙ ቀበሌ አገናኝ ሆኖ ሁለት ቀበሌዎችን የሚያገናኝ ከሆነ
- ደረጃ “ረ”፤የዉሃ ተቋሙ ከአንድ ጎጥ እስከ አንድ ቀበሌ ብቻ አገልግሎት የሚሰጥ

- ደረጃ “ለ” ፣የዉሃ ተቋሙ የእጅ ፓምፕ የተገጠመለት መለስተኛ ጥልቅ ጉድጓድ፣ የእጅ ጉድጓድ፣ ምንጭ በቦታዉ እና ባለመስመር ሆኖ በአንድ ቀበሌ ዉስጥ የሚገኙ እና በተቋማቱ የሚጠቀሙት ማህበር በቀበሌ ደረጃ ህብረት የፈጠረ ከሆነ

- ደረጃ “ሸ” የዉሃ ተቋሙ የእጅ ፓምፕ የተገጠመለት መለስተኛ ጥልቅ ጉድጓድ፣ የእጅ ጉድጓድ፣ ምንጭ በቦታዉ እና ባለመስመር ከሆነ ተብለዉ ደረጃ ይሰጣቸዋል፡፡

6 . በአንስተኛ የገጠር መጠጥ ዉሃ ተቋማት አስተዳደር ዙሪያ የተከናወኑ ተግባራት

- መመርያው ከወጣ በኃላ በ2008 በጀት ዓመት በአንስተኛ የውሀ ተቋማት146 የገጠር መጠጥ ዉሃ ተጠቃሚዎችን ማህበር ማደራጀት ተችሏል፡፡
- ማህበራት ሥራ የሌላቸው ውጣቶች እንዲቀጠሩ ተደርጓል፡፡
- ማህበራት የውሃ ታሪፍ በጠቅላላ ጉባኤ አፀድቋል፡፡
- ማህበራቱ የሚመራበት የውስጥ መተዳደርያ ደንብ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ተደርገል፡፡
- አብዛኛዉ ማህበራት የገንዘብ ቁጠባ የካፒታል መጠን እንዲያሳድጉ ተደርጓል፡፡

7. የተገኘ ውጤት

1. በኮሚቴ ድባክን የነበረው ገንዘብ በአብቁተ 250,000 መቆጠብ ችለዋል፡፡

2. 10 የገጠር መጠጥ ማህበራት 53 በዉሀ ዘርፍ የተመረቁ ሥራ የሌላቸው ወጣቶች እንዲቀጠሩ ተደርጓል፡፡

3. የሰራተኛ ቅጥር የፈጸሙ ማህበራትን አሁን የውሀ ተቋማትን የሚመሩ ሥራ አስኪያጅ ተቀጥሯል፡፡ የጥገና ባለሙያዎች ኦኘሬተሮች ተቀጥረው ገንዘቡ በአግባቡ እየተሰበሰበ ሲሆን የጥገና ሥራውም በማህበሩ እየተከናወኑ መሆኑን አረጋግጠናል፡፡

4. ማህበር በመሰረቱት ተቋማት ላይ አጥር እንዲኖራቸዉ፤ ዘበኛ የመቀጠር እንዲሁም ተጠቃሚዉ ባለቤት መሆኑን አረጋግጠናል፡፡

5. ቀበሌ አገናኝ የውሃ ተቋማት ለማስተዳደር ፈተና ሆኖ ነበር የቆየሁ በአሁኑ ሰዓት ተቃሎሉ ስራ አስፈፃሚ ከየቀበሌው የተውጣጣ ሆኖ ቅጥር ሰራተኞች ተቀጥሯል፡፡

6. በአነስተኛ የውሃ ተቋማት በቀበሌ ደረጃ ህብረት ፈጥረው ሥራ አስኪያጅ የተቀጠረበት ሁኔታ አለ

8. የመለዋወጫ አቅርቦትና የጥገና ስርአት ያሉ ችግሮችን ለመፍታት የተወሰደ መፍትሄ

- ይህንን ችግር ለመፍታት በቢሮ በኩል የመጠጥ ውሃ ተቋማት የመለዋወጫ ፣ መገጣጠሚያ እና የጥገና ማስፈጸሚያ የአሰራር ሞዳሊት አውጥቷል፡፡
- ይህ ሞዳሊት አስፈላጊነት
- በክልላችን በአሉት የውሃ ተቋማት የመለዋወጫና መገጣጠሚያ እቃዎች አቅርቦት ላይ የተሰማሩ ድርጅት በወረዳ ደረጃ ባለመኖሩ እና ተመጣጣኝ ዋጋ ያለውን በተፈለገው ጊዜ ማግኘት አለመቻል እና ሲበላሹ በወቅቱ ለመጠገን የመገጣጠሚያ እና መለዋወጫ እቃዎች ማግኘት አለመቻላቸውን ለመፍታት

- ማንኛውም መጠጥ ውሃ መለዋወጫ እና መገጣጠሚያ እቃዎች ግዥ ለመፈጸም እንዲሁም አፈፃፀሙንና ስርጭቱን ፤የጥገና ስርዓቱን ስኬታማ ለማድረግ በየወረዳው በውሃ ዘርፍ የሰለጡ ወጣቶችን በማደራጀት ለየውሃ ተቋሙ የተደራጁ ወጣቶች በጅምላ በመግዛት ለፈላጊዎች በችርቻሮ እንዲያቀርቡ ለማድረግ

9. ተግባራት

- በየወረዳ ከተማ የወረዳውን ስፋትና ጥበት መሰረት በማድረግ ከ3 እስከ 5 አባላት ያሉት ወጣቶች ተደራጅተው ተገቢውን የትምህርት ማስረጃቸውን አሟልተው ይቀርባሉ፡፡
- ወጣቶች በመስዋወጫና በመገጣጠሚያና አቅርቦትና ሽያጭን በተመለከተ እንዲሰለጥኑ ማድረግ፡፡/ሴቶች/
- ቢዝነስ ፕላን አዘጋጅተው ወደ ስራ እንዲገቡ ማድረግ፡፡
- የመሸጫ ቦታና አስፈላጊ ግባዓት እንዲሞላላቸው ማድረግ፡፡
- የብድር አቅርቦት እንዲመቻችላቸው ማድረግ፡፡
- ቅርበት ያለው ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፡፡

10. የሚጠበቁ ውጤቶች

- በክልሳችን በገጠር ያሉት የውሃ ተቋማትን የብልሽት ምጣኔን በከፍተኛ ደረጃ ስመቀነስ እና ሲበላሹም በጥራትና በሚፈለገው የመለዋወጫ እና የመገጣጠሚያ እቃዎች በማቅረብና በመጠገን ህብረተሰብ ተጠቃሚ ማድረግ እንዲሁም ውጤቶች ተጠቃሚ የሚሆኑበት ነው፡፡

- በክልሉ ባሉት ወረዳዎች በሙሉ ከ480እስከ 800 ወጣቶችን በውሃተቋማት መገጣጠሚያ እና መለዋወጫ እቃዎች አቅርቦት ተደራጅተዉ ገቢያቸዉን በማሳደግ ራሳቸውንና ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ ነው፡፡

ማጠቃለያ

- የውሃ ተቋማትን ለማስተዳደር የገጠር መጠጥ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበር መመሪያ በቢሮ የወጣ ሲሆን በቀጣይ በጀት ዓመት የተደራጀ ማህበራት ሥራ አጥ ወጣቶችን እንዲቀጥሩ እና ተቋማትን ቀጣይነት ባለዉ መልኩ ለተጠቃሚ እንዲያገለግሉ ይደረጋል፡፡
- የመለዋወጫ አቅርቦትና የጥገና ሥርዓት ሞዳሊቲው በቢሮ በኩል የተዘጋጀሲሆን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር/ ቴክኒክ፤ሙያ ኢንተር ፕራዞች ቢሮ፤ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ እና አብቁተ/ በቅንጅት ለመስራት ዝግጁነት ያለ ሲሆን ፤
- የቴክኒክ፤ሙያና የኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ ወጣቶች በሚሰማሩባቸው የንግድ መስኮች በኢንተርፕራይዝ እንዲደራጁ በማድረግ እናየተደራጁት ወጣቶች ህጋዊ ሰውነት እንዲኖራቸው ያደርጋል፤
- የዉሀ ፤መስኖና ኢነርጅ ቢሮ በመለዋወጫ እና የመገጣጠሚያ አቅርቦት ለተደራጁ ወጣቶች የስልጠና እገዛ በማድረግ ወደ ሥራ እንዲገቡ ይደረጋል፡፡
- አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም/አብቁተ/ ለወጣቶች በቂ ብድር ማቅረብ እና ለወጣቶች የተሠጠው ብድር ውጤታማ እንዲሆን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል
- የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ወጣቶች በተሰማሩባቸው የስራ መስኮች በቂ ድጋፍ ማግኘታቸውንና ውጤታማ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤ /የሴቶችስ/

Thank you